ከሥራ ተባረሃል? መብቶችህን ዕወቅ!

ፅሑፍ በወንድ ጾታ ቢጻፍም ለሁለቱም ጾታ ነው።

- **ከሥራ ከመባረርህ በፊት አነጋግረውሃል?** ሠራተኛን ከማባረሩ በፊት አሠሪው ጠርቶ የማስጠንቀቂያ ንግግር የማድረግ ግዴታ አለበት። በዚህም ሠራተኛን ከሥራ ማሰናብቱን በእውነት መገምገም ይቻላል። ይህ ግምገማ ከማስጠንቀቂያው ንግግር በኋላ እንደተባለው በከባድ አስተሳሰብና በጥንቃቄ እንጂ በማስጠንቀቂያው ንግግር ጊዜ አይደረገም። እንደ ማስጠንቀቂያው ንግግር ከሥራ ለመባረር ተጠባባቂ እንደመሆንህ መጠን የገቢ ምንጭህን/የቤተሰብ ሁኔታህ ከባድ መሆኑን እንዲያውም መረጃዎች በእጅህ እንዳሉ በማቅረብ ከሥራ እንዳትሰናበት መቃወም ይኖርብሃል። ከሥራ በመባረር ፈንታ በካምፓኒው ሊስማማህ ወደሚችል ሌላ የሥራ መስመር እንዲያዛውሩህ የመሳሰሉትን አማራጮች ተጠቀም። ሳያስጠነቅቁና መመሪያውን ሳይከተሉ በሚያሰናብቱ አሠሪዎች ላይ ከሥራ ለተሰናበቱ ሠራተኞች የካሣ ገንዘብ እንዲቀበሉ ፍርድ ቤቶች ከመፍረድ ወደ ኋላ አይሉም። ዕብራይስጥ የእናትህ ቋንቋ ካልሆነ በማስጠንቀቂያው ንግግር ጊዜ ቋንቋህን ተናጋሪ አስተርጓሚ እንዲሰጥህ የመጠየቅ መብት አለህ። ይዘቱ ያልገባህ የማስጠንቀቂያ ንግግሩ ዓላማውን ግብ አይመታም። ካለፉት ልምምዴ በአሠሪውና በአንተ መካከል የሚሆነውን የማስጠንቀቂያ ንግግር ቅዳው። በእጅ ስልካችሁ መቅዳት ትችላላችሁ። ለመቅዳት ደስ ላይላችሁ ይችላል፤ ግን አስታውሱ፣ ይህ የምትቀዱት ንግግር ሁኔታችሁን ሊቀይርና ለመብታችሁ መዝገብ ውስጥ ሊገባ ይችላል።

- **ለማስጠንቀቂያው ንግግር አስቀድመው አስታውቀውሃል?** አሠሪው አስቀድሞ ሊያስታውቅህ ይኖርበታል፤ አንተም ከሥራ እንዳትባረር ራስህን ለመከላከል የሚወክልህን ጠበቃና የተለያዩ መረጃዎችን ይዘህ የመቅረብ መብት አለህ።

- **እንድትባረር ከተወሰነ የስንብት ደብዳቤ ተቀብለሃል ወይ?** አሠሪህ ሥራ የጀመርክበትንና የተሰናበትክበትን ቀንና የስንብት ምክንያት ጠቅሶ የስንብት ደብዳቤ መሰጠት አለበት። ይህ ደብዳቤ ከኢንሹራንሽ መ/ቤት ከቢጡዋን ልዑሚ የመደጎሚያ ገንዘብ እንድትቀበል ይረዳሃል። ከአሠሪህ ካልተቀበልክ ሂደህ የሥራ ስንብት ደብዳቤ እንዲሰጥህ ጠይቅ።

- **ከሥራ ስትናበት የገንዘብ ካሣ ተከፍሎሃል?** ዓመት ለሞላው ወይም ዓመት ሊሞላው የተቃረበ ሠራተኛ ከሥራ ሲሰናበት የገንዘብ ካሣ የመቀበል መብት አለው። «ዓመት ሊሞላው የተቃረበ» ማለት ምን ማለት ነው? ህጉ ይህን አይገልጸውም። የፍርድ ውሳኔው ግን 11 ወራት እንዲሁም ከ10 ወራት በኋላ ከሥራ መሰናበትን እንደሚያጠቃልል ያብራራል። ይህም አሠሪው የሥራ ስንብት ካሣ ላለመክፈል ሲል ሠራተኛውን አሰናብቶ በምትኩ ሠራተኛ ፈልጎ መቅጠሩን ማረጋገጥ ከተቻለ ነው።

- **ከሥራ የተሰናበትከው ካምፓኒው ሠራተኛን ለመቀነስ ሲል ነው ያሰናበተህ?** አሠሪው ወጪን ለመቀነስ ሲል ያሰናበተህ ተገዶ ከሆነ ፍጹም እውነት ብለህ አትውሰደው። አንዳንዴ አሠሪው ደሞዝ የምከፍለው ገንዘብ የለኝም ቢለን ከሥራ የመሰናበት ዕድሌ ስለሆነ ምንም ማድረግ አልችልም ማለት የለብንም። ነገሩ ግን እንዲህ አይደለም! አሠሪው የምከፍለው ገንዘብ የለኝም ከሚለው ምክንያት ሌላ ተጨባጭ ምክንያት ማቅረብ ይኖርበታል እንጂ የገንዘበ እጥረት አለብኝ የሚለው ምክንያት ብቻውን በቂ አይደለም። እንዲሁም የገንዘብ ዕጥረት የሚለው ምክንያት በሌላ የካምፓኒውን ፕሮቶኮል፣ ሪፖርቶችና በመሳሰሉት ተጨባጭ መረጃዎች መደገፍ ይኖርበታል። «መቀነስ» ማለት ብቻ በቂ አይደለም። ተዓምራዊ ቃል ሳይሆን ጎን ለጎን ለስንብቱ እውነተኛ ምክንያት ያስፈልጋል።

- **አንተና ጎደኞችህ በአንዴ ነው የተባረራችሁ?** በአንድ ላይ ሁላችሁን ከሥራ ካባረራችሁና በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መብታችሁ ባይከበሩ የሚከተለውን ማድረግ ይቻላል፦

   1) በኅብረት ክስ ጊዜ(ብዙ ሠራተኞች አንድ ጠበቃ ከቀጠሩ)

   2) ሠራተኛን የውክልና ክስ(ከሥራ የተሰናበተ ሠራተኛ በሌሎች ተጨማሪ ሠራተኞችን ወክሎ በስማቸው ሲከስ የውክልና ክስ ለማቅረብ ሁኔታዎችን ማሟላትና የውክልና ክስ መሆኑን በፍርድ ቤት ማረጋገጥ አለበት)

* ከላይ የተባለው ሁሉ የተለየ ሁኔታንና ተጨባጭ መረጃን በጠለቀ ሁኔታ ሳይጠቅስ ስለሆነ አሁንም ሆነ ወደፊት የሚሆንን የፍርድ ጉዳይ ምክርን ልዋጭ አይሆንም። ይህን ወይም ሌላ ርምጃዎችን ከመውሰድ እንድትቆጠቡ ለመደገፍም አይደለም። በተባለው ላይ በሆነ መንገድ የሚደገፍ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሚያስከትለው ውጤት ራሱ ኃላፊነትን ወውሰድ ይኖርበታል። ስለፍርድ ቤት ጉዳይ ምክር በስልክ 02-6222335 በመደወል ወይም በኢ_ጦማር Adi@hacohenwolf.com በድኅረ ገፅ www.hacohenwolf.com ማግኘት ይቻላል።